# ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

*ዴሞክራሲያ ቅጽ* 39 *ቁጥር* 1 *መስከረም* 2006 *ዓ.ም*


## <u>እንኳን ለ2006 ዓ. ም አዲስ ዓመት አደረሳችሁ</u> !

*ኢሕአፓ፣ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ በማለት መልካም ምኞቱን ይገልጻል:: ኢትዮጵያ ጥንታዊትና ታሪካዊት መሆኗን ከሚያረጋግጡላት ዐበይት ማስረጃዎች መካከል፣ በራሷ ፊደልና የዘመን አቆጣጠር ተጠቃሚ መሆኗ ነው:: በራሷ የዘመን አቆጣጠርና የጊዜ ቀመር መገልገሏ ደግሞ፣ የራሷን ሥልጣኔ መሥርታ፣ ህልውናዋንና ነፃነቷን ጠብቃና አስከብራ እንድትኖር አስችሏታል:: ይህም በበኩሉ ላልተጻቀለውና ላልተበረዘው፣ ላልተበከለውና ላልተሸመደመደው ታሪኳ፣ ባኅሏና ነፃነቷ መሠረት ሆኖ ቀይቷል:: በየዓመቱ ዘመን፣ በሀገራችን የዘመን አቆጣጠር ቀመር ሕግ በመገዛት ይለወጣል:: በባህልና በልምዱ መሠረትም፣ ዜጎቿ እንደየዕምነታቸውና አምልኳቸው ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ በሠላም አብሮ በመኖራቸውና ለአዲሱ ዘመን አብረው በመድረሳቸው ምክንያት ደስታቸውንና መልካም ምኞታቸውን በአክብሮትና በመተባባበር እየገለፁ የአዲሱን ዓመት መባቻ በጋራ ያከብሩታል:: ይህም ለዘመናት በዜጎች መካከል በሰላም አብሮ የመኖሩን ባህልና ልምድ አዳብሮትና አጠንክሮት ቆይቷል:: የወደፊቱንም የጋራ ትስስርና ተስፋ እንዲካፈሉ እያደረገ አቆይቷቸዋል:: ተጠቃልሎ ሲታይም፣ እስከዛሬ ድረስ ፀንቶ ለቆየው ሀገራዊና ሕዝባዊ አንድነት እንዲሁም የሀገር ነፃነትና ሉዓላዊነት አብነትና መሠረት እንደሆነ መገንዘብ አያዳጋትም:: ይህም ሐቅ የወያኔ መሪዎች፣ "የኢትዮጵያ፣ ታሪክ ያንድ መቶ ዓመት ታሪክ ነው" የሚሉትን ከንቱ ቅዠትና ቅሌት ዋጋ ቢስ ያደርገዋል::*

*ዘመናት፣ ወቅታቸውን እየጠበቁ መፈራረቃቸው የተፈጥሮ ሕግ በመሆኑ፣ በየዓመቱ እንደ አዲስ ይለዋወጣሉ:: የእነርሱ መፈራረቅ አዲስ የተሻለ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጥ ካላስገኘ ግን ፣ በሕዝቡ ሁለንተናዊ ኑሮ ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም:: በሕዝቡ ሕይወት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ካላስገኘ ደግሞ የዘመን መለዋወጥ ብቻውን ትርጉም ያለው ልዩነት አያመጣም:: የጥንቱን- የጧቱን የሀገራችንን የዘመናት ለውጦችና የታሪክንም ሂደት ለጊዜውም ቢሆን እናቆየውና ፣ ከአስራ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ስድስት* (1966) *ዓ.ም ወዲህ፣ ማለትም፣ በአለፉት አርባ ዓመታት ውስጥ ብቻ ያለፉትን ማየት እንችላለን:: እነኝህን የታሪክ ሂደቶች ደግሞ፣ በሚገባ ማጤን ከተቻለ፣ ከአንደኛው ጽንፍ እስከ ሌላኛው ጽንፍ ድረስ የተፈራረቁትን የሥርዓት ለውጦች መመርመር አያዳግትም:: ይህ ከሆነ ዘንዳ ፣ እነኝህ ለውጦች፣ ዴሞክራሲ ሥርዓትን ለማስፍን ምን ያመጡት ፋይዳ አለ? ለሚለው ጥያቄ አግባብ ያለው መልስ መስጠት እንችላለን:: በነኝህ ሦስት የሥርዓት ለውጦች ሂደት ፣ የሕዝብን ነፃነትና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አስመልክቶ፣ ከቶ የመጣ ለውጥ የለም::*

ለአለፉት አርባ ዓመታት በአገራችን ኢትዮጵያ፣ በስምና በቅርፅ እንጅ፣ በአገዛዝ ዘይቤ እምብዛም ልዩነት የሌላቸው አምባገነን ሥርዓቶች ተፈራርቀዋል:: ከንጉሣዊ ፊላጭ-ቆራጭ ሥርዓት ጀምሮ የወታደራዊውን ጁንታ አካትቶ እስከ ዘረኛው የወያኔ አምባገነን ቡድን ያለውን ስንመለከት፣ ሁሉም ፀረ-ዲሞክራሲና ፀረ-ሕዝብ ሥርዓቶች ናቸው:: የአምባገነን ሥርዓታቸውን አጠናክረው የሥልጣን ዘመናቸውን በአሰተማማኝ ደረጃ ለማራዘም፣ ማንኛውንም የመጨቆኛ መሣሪያ ሁሉ በመዳፋቸው ውስጥ በማስገባት ሕዝቡን ያለ ማፈናፈን ይገዛሉ:: ለሥርዓታቸው ማኀልበቻ ሲሉም፣ ለማፈኛ የሚረዷቸውን ህጎችና ደንቦች ዘርግተው ይጠቀማሉ:: ተቃዋሚዎቻቸውን ሁሉ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ሲሉም የፖለቲካ ምኅዳሩን በማጥበብና በማጨናነቅ ይገለገሉበታል:: ለእነርሱ በሚጠቅማቸው መልኩ በሚያወጡት የሕግ ድባብ፣ ማንኛውንም የተቃውሞ እንቅስቃሴ ሁሉ እያከሰሙ ለማጥፋት ይጠቀሙበታል:: በነኝህ ሦስት ተፈራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች ፣ አርባ አዳዲስ አውደ ዓመታት ተለዋውጠዋል ፣ አርባ መስከረሞችም እየመጡ ሄደዋል:: ያም ሆኖ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወትና የኑሮ ደረጃ ፣ ነፃነትና ፍትሕ-ርትዕ፣ የኢኮኖሚ ብልፅግናም ሆነ በዕድገት መሻሻል በኩል የረባ ውጤት አልተመዘገበም:: ዘላቂ ሠላምም ሆነ የፖለቲካ መረጋጋት ለአገሪቱ ዋስትና ሊሆኑ አልቻሉም:: የዴሞክራሲ ሥርዓት ተመስርቶ፣ የሕግ የበላይነት ሰፍኖ፣ የዜጎች ሰብዓዊ መብቶች ተከብረው አይታዩም:: አምባገነን በሰፈነበት ሥርዓት ስር የሚገዛ ሕዝብ፣ ለመብቱና ለነፃነቱ አይከፍሉ ዋጋ በመክፈል ነፃነቱን እስኪያስመልስ፣ በሀገሪቱ ውስጥ ሠላምና መረጋጋት አይመጣም:: ገዥዎቹ፣ ሕዝቡን ሰጥ ለጥ አድርገነዋል ብለው ራሳቸውን ቢደልሉምና ብሎም፣ አንፃራዊ ሠላምና መረጋጋት አግኝተናል ብለው የቀቢፀ-ተስፋ ምኞት ቢያድርባቸውም እንኳ፣ የሕዝብ ቁጣ ገንፍሎ ከመጣ፣ እንደ ቋያ እሳት እነርሱን አቃጥሎ፣ የተሻለ ሠርዓት እንደሚያመጣ ታሪካዊ ሐቅ ነው::

በአርባ ዓመታት የተፈራረቁት የአምባገነን ሥርዓት አራማጅ መሪዎችን መጨረሻ ስንታዘብ፣ ሦስቱም ከፖለቲካው መድረክ የተወገዱት፣ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለሕዝብ በማስረከብ ሳይሆን ፣ አንዱ፣ በዕድሜ መጥገብ ፣ ተከታዩ ደግሞ ፣ አገር ጥሎ በመሸሽ ሦስተኛው ደግሞ በሞት ቅስፈት መሆኑን የምንገነዘብ ከመሆኑ በላይ አንድ መሠረታዊ ሐቅንም እንረዳለን:: ይኸውም ፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ፣ መሪዎች ነን ብለው የሚመጡት ሁሉ ምን ያህል የሥልጣን ጥመኞች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ካልተገደዱ በስተቀር፣ በምንም መንገድ ቢሆን ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው የማይተው መሆናቸውንም ጭምር ነው:: እስካሁን እንደታየው ፣ የእነኝህ ሥርዓቶች አራማጆች ሥልጣን ይዞ ለመቆየት የሚጠቀሙበት የየራሳቸው የማታለያ ምርኩዝ ነበራቸው:: የመጀመሪያው ፍትሀ-ነገሥት፣ አፄውን የተካው የሕዝብ ሥርዓት፣ የመጨረሻው ደግሞ የብሔር ነፃነት የሚሉ ናቸው:: በነዚህ የአፍዝዝ-አደንዝዝ ምትሃት ፕሮፓጋንዳ ፣ የአምባገነን ሥርዓቶቹ ሲፈራረቁ ቆይተዋል:: ዛሬ፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የፖለቲካ ነቃተ-ኅሊናው በተሻለ ደረጃ ስለሚገኝ፣ ማንም አልኩ-ባይ መሰሪ እያታለለ ሊገዛው ከማይችል ደረጃ ላይ በመድረሱ፣ በሀገራችን የፖለቲካ መልከዓ-ምድር፣ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መምጣትና መስፈን አስተማማኝ ነው ተብሎ ይታሰባል::

ነገር ግን፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት ዕውን መሆን፣ በኃሳብና በምኞት ብቻ የሚፈፀም አይሆንም:: የዜጎች መብትና ነፃነት በግለሰብ ደረጃ መከበር ያለበት መሆኑ፣ የተፈጥሮ ፀጋ ነው እስከተባለ ድረስ፣ ያን መብትና ነፃነት ለማግኘት እያንዳንዱ ዜጋ መታገል አለበት:: እያንዳንዱ ዜጋ፣ እራሱ ታግሎ ነፃነቱንና መብቱን ማረጋገጥና ማስከበር ይኖርበታል:: በግለሰብም ደረጃ ይሁን በድርጅት ተሰባስቦ ታግሎ ነፃነትን

*የማስከበሩ ጉዳይ ለውይይት የሚቀርብ ነገር አይደለም:: ለዘመናት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርሱ ራሱ የሕይወት ዋጋ እየከፈለ ነፃነቱን ከውጭ ወራሪ ኃይሎች ጋር እየታገለ ማቆየቱን ማንም ሊነገረው የሚገባ ጉዳይ አይደለም:: ከውጭ ጠላቶችና ወራሪ ኃይሎች እየተፋለመ የአገሩን ነፃነት አስክበሮ እንደኖረው ሁሉ ፣ ከሀገር-በቀል አምባገነኖች ታግሎ የራሱን ነፃነትና መብት ማስከበር እንደሚገባው ጠንቅቆ ያውቃል:: <u>የነፃነት ዋጋ፣ ነፃነት ብቻ</u> <u>መሆኑን ፣ የነፃነቱ ጌታ ከሆነው ከኢትዮጵያ ሕዝብ የበለጠ ሌላ የሚያስገነዘበው አይኖርም</u>::*

*በሀገራችን የአዲስ ዓመት በአሮጌው መተካት ብቻውን ምንም ለውጥ እንደማያመጣ እሙን ሆኗል:: የዘመናት ለውጦች የሚያጓጉትና የሚናፈቁት በሀገርና በሕዝብ ዘንድ በተሻለ ለውጥ ላይ የተመሠረተ አጥጋቢ ውጤት ማስገንዘብ ሲቻል ነበር:: ይህ በሀገራችን የህልም እንጀራ እንደሆነ አለ:: ጉልቻዎቹ ተለዋወጡ ማለት የተሻለ ለውጥ መጥቷል ማለት አይደለም:: የአምባገነኖች ልውውጥ፣ "ትሻልን ሰድጄ ትብስና አመጣሁ" ከሚለው ብሂል አያልፍም:: ለሀገራችንም ሆነ ለሕዝባችን አጥጋቢ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው፣ በዕርግጥ ሕዝቡ የዴሞክራሲ ሥርዓትን ተጎናጽፎ የሥልጣን ባለቤት ሲሆን ብቻ ነው::*

*በዴሞክራሲ ሥርዓት የሚተዳደሩ መንግሥታት፣ በየአዲሱ ዓመት መግቢያ ላይ፣ የሥራ ዕቅዳቸውንና የልማት ፕሮግራማቸውን ለሚመሩት ሕዝብ ይፋ ያደርጋሉ:: በተገባደደው ዓመት ያካናወኑትን የሥራ ውጤት፣ በብሔራዊ ምክር ቤቶች በኩል የተሟላ ዘገባ ለሀገሪቱ ዜጎች በይፋ ያሳውቃሉ:: ሳይፈፀሙ ለቀሩት ጉዳዮች ደግሞ፣ ለምን እንዳልተሳካላቸው አጥጋቢ ነው በሚሉት ምክንያት ያስረዳሉ:: የተግባራቸው ውጤት ፈራጅ-ዳኛ፣ የመረጣቸው ሕዝብ ነውና፣ ዘገባቸውን፣ የመቀበል፣ የመንቀፍና ያለመቀበል መብቱ የተጠበቀ ነው:: ሕዝቡ ካልፈቀደ ከሥልጣናቸው ያወርዳቸዋል:: የመጨረሻ የሥልጣን ባለቤት የሀገሩ ዜጎች በመሆናቸው ፣ መሪዎቹ፣ ከዜጎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በግልፅነትና፣ ተጠያቂነት ላይ በተመሠረተ የሕግ ድባብ ላይ ይሆናል:: ማንኛውም መንግሥታዊ ሥልጣን ሁሉ፣ በሕግ ልጓም የተሸበበ ነው:: ለመንግሥት ሥልጣን ከሚያበቁት ዓይነተኛ መስፈርቶች መካከል፤ ዋናዎች፣ ችሎታ/ክኅሎት፣ የሙያ ብቃት፣ ተግባርና ሥነ ምግባር፣ የሀገርና የሕዝብ ታማኝነት የመጀመሪያውን ረድፍ ይይዛሉ:: ለብሄራዊ ጥቅም ቀናዒ መሆናቸውንም ያላንዳች ማመንታት ያረጋግጣሉ::*

*ይህ አሰራርና ልምድ፣ የዴሞክራሲ ትርጉም፣ ተመክሮና አፈፃፀም በመሆኑ፤ ራሳቸውን ከአምባገነን ሥርዓት ነፃ ያደረጉ የዓለም ዜጎች ሁሉ ይጠቀሙበታል:: ይገለገሉበታል:: የሚኖሩትን ኑሮ ብቻ ሳይሆን፣ የወደፊቱ ሕይወታቸውንም ይሁን ራዕያቸውን እያማተሩ፣ ዕቅዳቸውን እየቀየሱ ያረጋግጡበታል:: ይተማመኑበታል:: የዴሞክራሲ ሥርዓት፣ የሕዝብ ነፃነትና መብት፣ የዕድገቱም ዋስትና ማረጋገጫ ነው ተብሎ ስለታመነበት፣ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ ለመንግሥት ሥልጣን ገደብና ልኬታ እንዲኖረው በሕግ የተወሰነ ይሆናል:: ሚዛኑ የተጠበቀ የሥልጣን ቁጥጥር መኖሩ፣ አምባገነን እንዳያቆጠቁጥ (ለመቆጣጠር) የሚያስችል ዘዴ ነው ተብሎ ይታመናል::*

*በመሆኑም፣ ሥልጣንን፣ በዘር ሐረግ፣ በብሔር ተዋፅዖ፣ በጎሳ ጥልፍልፍ፣ በቤተሰብ ዝምድና፣ በጋብቻና አምቻ ፣ በክልልና በቡድን ትውውቅ፣ አዋቅሮና ጠርንፎ ኢትዮጵያንና ዜጎቿን እያጠፋ የሚገኘው ወያኔ፣ ዴሞክራሲ በሀገሪቱ ሰፍኗል እያለ ይቀልዳል:: መቀለድን እንደ ሰብዓዊ መብት ቆጥረው የሚያጫፍሩቱ፣ የዳንኪራው*

ተሳታፊዎች ቢሆኑ አያስደንቅም:: በላይኛው አንቀጽ ለመግለፅ እንደተሞከረው ግን ዴሞክራሲና የወያኔ ዘረኛ ሥርዓት አጥፊና ጠፊዎች እንጅ አብረው የሚኖሩ አይደሉም:: ያንዱ መጥፋት ለሌላው መኖር ዋስትና በመሆኑ፣ ወያኔ ዴሞክራሲን አጥፍቶ ብቻውን እየኖረ ነው:: ወያኔ፣ "የምርጫ" ብቸኛ ተወዳዳሪ በመሆን ብቸኛ "አቸናፊ" ስለሆነ፣ ዴሞክራሲን አጥፍቶ አምባገነንነትን ለማስፈን ማጠየቂያ ሆኖታል:: ይህም በበኩሉ፣ ለኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ጠላቶች ፍስሐ-ሀሴት ሆኗቸዋል:: ለእነርሱ ጥቅም አስጠባቂ፣ ከወያኔ መሪዎች የበለጠ ታማኝ አጋፋሪና ሰይፈ-ጃግሬ የላቸውምና !

በሀገራችን፣ የአዲስ ዓመት መምጣትና መሄድ ፣ የመሪዎቹም ሀገር እያጠፉ መኖርና በመጨረሻውም የእነርሱ መጥፋት፣ እንደ ተለምዶና ተፈጥሮ ክስተት እየታየ ይኸውና ከዓርባ ዓመታት በላይ ሆኗል:: አሮጌው አምባገነን ሲጠፋ ሌላ አዲስ አምባገነን እየተተካ በአዲስ ጥርሱ ጋግጦ ሲጨርስ ወደ እሚሄድበት ይሄዳል:: ተተኪው ደግሞ የተሻለ ሆኖ ስለማይገኝ ፣ አሁንም "ትሻልን ሰድጀ ትብስን አመጣሁ" በማለት ሕዝቡ መራራ ሕይወቱን ይቀጥላል:: ኢትዮጵያና ሕዝቧ ጠንካራ አለት ናቸውና እንደ ጂብራልታር ደሴት ማንኛውንም የጥቃትና የበደል ማዕበል እየተቋቋሙ ይኖራሉ ማለት ይቻል ይሆናል፣ ያም ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ የተቃጣው አደጋ ከዚህ በከፋ ሁኔታ አይከሰትም ማለት ግን የሚቻል አይመስለንም::

እስካሁን ድረስ፣ ኢትዮጵያና ሕዝቧ በአንድ ላይ የቆዩትና ወደፊትም ፀንተው ይቆያሉ ተብሎ ተስፋ የሚጣለው፣ መሠረታቸው ፅኑ በመሆኑ ነበር:: ይህ ፅኑ መሠረታቸው ግን በወያኔ ዘረኛ ሥርዓት በመናጋት ላይ ይገኛል:: ሕዝብ እንደ ሕዝብ አገርም እንደ አገር ሊከስሙና ሊጠፉ አይችሉም ብሎ መፅናናት፣ የዓለምን ታሪክ በሚገባ ካለመረዳት የሚመጣ መዘናጋት ይሆናል:: በዓለም የረዥም ጊዜ የታሪክ ሂደት፣ ብዙ አገሮችና ሕዝቦች እንዳልነበሩ ሆነው መቅረታቸው እየታወቀ፣ ይህ ዕጣ-ፈንታ ኢትዮጵያን አይመለከታትም ማለት አንችልም:: ዉሃ የሚወስደው እያሳሳቀ ስለሆነ፣ የወያኔ ዘረኛ ሥርዓት ኢትዮጵያን ቀስ በቅስ በዘር እየከፋፈለ አጥፍቶ እንደሚያጠፋት አለመረዳት የጥፋቱ ተባባሪ ከመሆን ተለይቶ አይታይም:: የዘመናት መፈራረቅ የተፈጥሮ ሕግ በመሆኑም፣ እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የሚመጣውን በተስፋ ከመቀበልና የሚሄደውንም በትዝብት ከመሸኘት በስተቀር ሌላ አማራጭ አላገኘም:: እስካሁን ድረስ፣ አዲስ አምባገነን ሲመጥ በተስፋ የሚጓጓውና በአርምሞም የሚታገሰው፣ ምናልባት ከወደቀው አምባገነን የተሻለ ሁኔታ ይፈጠራል ከሚል ከቀቢፀ-ተስፋ አኳያ ነበር:: ይህ ተስፋው ግን ከመቅፅብት እንደጤዛ ይረግፍበታል:: በመሆኑም የዘመናት መፈራረቅ ብቻ ለሀገራችንና ለዜጎቿ የሚያመጣው ፋይዳ አይኖረውም::

አምባገነኖች በታሪክ የሕዝብን ዘር ለማጥፋት የተለያዩ መንገዶችን ሲጠቀሙ ኖረዋል:: ብዙሃኑን የሚያጠፋ የጦር መሣሪያ ከመጠቀም ጀምሮ፣ የጋዝና መርዝ ጭስ ማዝነምን ጨምሮ፣ እንደ ናዚ ጀርመን በሚሊዮን የሚቆጠሩትን በኮንሴንትሬሽን ካምፕ እያጎሩ በረሃብና ቸነፈር እያሰቀዩ መጨፍጨፍ፣ ሊጠፋ የሚፈልጉትን ሕዝብ ሴቶች እንዳይወልዱ የሚያመክን መድኃኒት መርፌና ክኒን እያስገደዱ መውጋትና መጋት ሁሉ አስቃቂ ድርጊቶች ናቸው:: የአማራውን ሕዝብ ቁጥር ለመቀነስና ከተቻለም ዘሩን ለማጥፋት የሚደረገው የጭካኔ ድርጊት ብዙ የፖለቲካ ታዛቢዎችና የሰብዓዊ መብት ተንከባካቢ ድርጅቶችን በየጊዜው የሚያቀርቡት ጩኸት መስማት ብቻ ይበቃል:: አንድን ሀገር፣ ሀገር ነው ተብሎ የሚያስጠራው፣ በምድሪቱ የሚኖረውን ሕዝብ ሲያካትት እንጅ ባዶው መልከዓ-ምድር ብቻ አይደለም::

ጨካኞች፣ ምድሯን እንጅ፣ ሕዝቡን አንፈልገው የሚሉትም፣ አንድን ሕዝብ ለማጥፋት ከመነጨ አመለካከት/ፖሊሲ ነው።

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው አሮጌው በአዲስ ዓመት እየተተካ ዘመናት ቢፈራረቁም አሁንም፣ የሕዝቡ መከራና ስቃይ፣ ረሃብና በሽታ፣ ድኅነትና ጉስቁልና ጭቆና እስራትና ስደት በከፋ መልካቸው እንደቀጠሉ ናቸው። አዲስ አምባገነን ሲመጣ ደግሞ፣ የተረከበውን ጥፋት ከማባባስ በስተቀር፣ የተሻለ ለማምጣት አይፈልግም። ሀገር አጥፍቶ እራሱ ሲጠፋ ደግሞ፣ ለመልካም ትዝታ እንኳን ሊሆን የሚችል አንዳች በጎ ነገር ሳይተው ይሄዳል።

የኢትዮጵያ ገዥዎች፣ ዘመን ሲለወጥ፣ ለአዲሱ ዓመት የሚሆን የሥራ ዕቅድና የልማት ፕሮግራም በሚል የከንቱ ፕሮፓጋንዳና የባዶ ተስፋ ንግግር ያሰማሉ። ባለፈው ዓመት በተግባር አዋልነው የሚሉዋቸው የኢኮኖሚ ክንዋኔዎች፣ የሰፊውን ሕዝብ ኑሮ በመሠረታዊ ደረጃ ያሻሻሉ ባለመሆናቸው ፕሮፓጋንዳው የብዙሃንን ጆሮ ሊስብ አይችልም። ባለፈው ዓመት ስንት ወኅኒ ቤቶች እንደሰሩ ፣ ምን ያህል የተቃዋሚዎቻቸውን ማጎሪያ ካምፖች እንደገነቡ ፣ ስንት አዳዲስ ሰላዮችንና አፋኝ ጓዶች አሰልጥነው እንዳሰማሩና ስንት ተቃዋሚዎቻቸውን በቁጥጥር ስር አድርገው እንዳሰቃዩ ግን አይገልፁም። ይህ ሁሉ ደግሞ ፣ የሀገርና የሕዝብ ጥፋት እንጅ በጎ ነገር እንዳልሆነ ፣ ባለ ጤና እዕምሮ የሆነ ዜጋ ሁሉ አይስተውም።

ይህን አዲስ ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲቀበለው፣ በሀገራችን፣ የፍትኀ-ርትዕ መከበርን፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት መምጣትን፣ የዜጎች እኩልነትና አንድነት መረጋገጥን፣ የሀገራችን ሉዓላዊነት መከበርን በመፈለግና በመመኘት ነው። የእኛም ያልተቋረጠ ትግል ያተኮረው በእነኝህ ዐበይት ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ነው። ይህን ዕውን ለማድረግ ሲባልም ከባድ መሥዋዕትን የሚጠይቅ ፣ እልህ አስጨራሽ ትግል አድርገን ያንኑ ቀጥለናል። ለባዕድ ቅኝ ግዛትም ይሁን ለሀገር-በቀል ጨቋኞች የማይበገረው የኢትዮጵያ ሕዝብም ፣ የነፃነት ዋጋ ነፃነት ብቻ መሆኑን ስለሚያምን፣ ነፃነትን ለማግኘት በዚህ አዲስ ዓመት፣ ሁል-አቀፍ ትግሉን ማፋፋሙን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። በበኩላችን በዚህ አዲስ ዓመት፣ ለድል የሚያበቃ የትግል ዘዴያችንን እያስተካከልን እንደምንቀጥል ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ቃል-ኪዳናችንን እናድሳለን። ለሕዝባችንም በአዲሱ ዓመት መልካሙን ሁሉ እንመኛለን !

ኢትዮጵያ አገራችን በነፃነት ለዘለዓለም ትኖራለች !
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !

የወያኔን አገዛዝ ለማውደም በጋራ እንነሳ፤ እንታገል!
እናቸንፋለን !!